የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)
Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)
www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com

# HR 128 መጽደቅ ለመሰረታዊ የሙብት ትግላችን ታላቅ ድጋፍ ነው
# ሸንጎ ህጉን ይደግፋል፤ ለተፈጻሚነቱም ተግቶ ይሩለማል

HR 128 ተብሎ የሚታወቀው ባሜሪካ ኮንግረስ (ፓርላማ ) ውስጥ ለውሳኔ ቀርቦ የነበረው በኢትዮጵያ መንግስት የሙብት አያያዝ ላይ ያተኮረ የህግ ረቂቅ እነሆ ትናንት መጽደቁ ተነገረ። በውጭ አገር ያሉ የሰብዓዊ መበት ተከራካሪዎችና የተደራጁ ኢትዮጵያውያን ይህ የህግ ረቂቅ እንዲጸድቅና በስራ ላይ እንዲውል ለረጅም ጊዜ ከፍተኛ ተጋድሎ ሲያድርጉ ቆይተዋል። ሸንጎ ለዚህ ስኬት ታጥቀው ለታገሉ ሃይሎች በሙሉ ያለውን አድናቆትና ክብር እያስታወቀ፤ የረቂቁ ህግ ሆኖ መጽደቅ ለኢትዮጵያ ህዝበና ለመላው የዴሞክራሲ ሃይሎች ታላቅ ድል መሆኑን ይገልጻል።

ይህ ህግ ካካተታቸው ዋና ዋና ድንጋጌወች ውስጥ፤

- አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲነሳ በግልጽ ይጠይቃል
- በተለያዩ ክልሎች በመንግስት የጸጥታ ሃይሎች የተፈጸሙ ግድያዎች በገለልተኛ አካል እንዲጣሩ ይደነግጋል
- መሰረታዊ ሰብአዊ ሙብቶች በተለይም የሚዲያ ነጻነት ና ሀሳብን በነጻ የመግለጥ ሙብት እንዲከበር አጥብቆ ይጠይቃል
- የሰብአዊ ሙብት ጥሰት ያካሄዱ በተለይም የገደሉና ሌሎችንም ስቃዮች የፈጸሙ ወንጀላቸው ተጣርቶ ለፍርድ እንዲቀርቡ ያወሳል
- በቀጣይነትም የመንግስት የጸጥታ ሀይሎች ተመጣጣኝ ያልሆነ እርምጃ መውሰድ እንዲያቆሙ ወዘተ የሚያስገድዱ ድንጋጌዎች ይጨምራል
- አዲሱ ህግ የኢትዮጵያ መንግስት ቢያፈነግጥ ወይም ይህን አላደርግም ቢል እንደማስገደጃ ሆነው ሊጠቅሙ የሚችሉ የተለያዩ እርምጃዎችን ለመሳሌ ማእቀብ መጣል እርዳታ መከልከል ወዘተ ማስገደጃወችን ያካተተ ነው።

የኢትዮጵያ መንግስት በዓመት እስከ 3 ቢሊዮን ዶላር የሚደርስ እርዳታ ከአሜሪካ መንግስት ስለሚቀበል ይህን ከፍተኛ እርዳታ እንዳያጣ ይህን ህግ ሳይወድ ተግባር ላይ ለማዋል ይገደዳል የሚል አንደምታ አለ። አሁን እንግዲህ ህጉ ስለጸደቀ ሀገራችን ውስጥ ሰብአዊ ሙብትን ለማስከበር ታላቅ ድጋፍን ለህዝባችን ይሰጣል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ዶክተር አብይና ደጋፊወቻቸውም መሰረታዊ የሙብት መከበርን፣ የህግ የበላይነትን ወዘተ ለማስከበር ቆርጠናል ብለው በተናገሩት መሰረት የሰጡትን ቃል ጠብቀው ተግባራዊ ለማድረግ በመንቀሳቀስ ይህን ድንጋጌ መቀበላቸውን ሊያሳዩን ይገባል። ይህንንም በይፋ ቢያሳውቁ ለህዝባችን ሙብት መከበር ያላቸውን ፍላጎትና ቁርጠኛነት ይበልጥ ያሳያል፣ ይበልጥ የህዝብ ድጋፍም ያስገኝላቸዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com

ሸንጎ ከአገራችን ዜጎች ጎን ቆሞ ለሁላችንም መብት መከበር አሁንም ጠንክረን መታገል እጅግ አስፈላጊ ነው ብሎ ያምናል። በውስጥም በውጭም የሚደረገው ሰላማዊ ትግል ውጤት እያስመዘገበ ቢሆንም ገና የሚፈለገውን ግብ አልመታም፤ የምንፈልገውን መብት አላጎናጸፈንም። ለዚህም ነው እንደ ቀደምት ተማሪወች አሁንም

“ነጻነት ነጻነት የምትሹ

ታገሉለት አትሸሹ”

የሚለውን መፈክር ከፍ አድርገን በማሰማት ትግሉን አጠናክሮ መግፋት ያለብን፡

የተባበር ትግል ያሸንፋል!

ለሰብዓዊ መብታችን፤ ለፖለቲካ ነጻነታችን ሳናሰልስ እንሚገታለን !